# ፕራየር ኢቪክስን እና ክሬዲት ሪፖርት

## ተከራዮች ፡ መብቶቻችሁን እወቁ!

### በሚከተሉት ምክንያቶች ከመኖሪያ ቤትዎ ሊከለከሉ ወይም ሊባረሩ አይችሉም ...

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ዘር ፣ ብሄር ወይም ብሄራዊ አመጣጥ | አካል ጉዳተኝነት | ሃይማኖት | የቤተሰብ ሁኔታ | የጾታ ማንነት ወይም የወሲብ ዝንባሌ |

### በርስዎ ላይ ይሄ ከተከሰተ ፣ የማስወጣት መብት ጋር በመደወል ምክር ያግኙ ።

## ክሬዲት ሪፖርት ምን ማለት ነው? የጀርባ ህይወት ምርመራ ይለያል?

**ክሬዲት ሪፖርቶ የፋይናንሻል ታሪክዎ ማህደር ነው።** በውስጡ **ፍጆታውን በሰዓቱ መክፈልዎን** ፣ **ክስረት ማሳወቅዎን** እና **ለብድር ወይም ክሬዲት ካርድ አመልክተው** መሆኑን መረጃ ያካትታል።

**የጀርባ ህይወት ምርመራ** ወይም በሌላ ስሙ **የጀርባ ህይወት ማጣራት** ይባላል ፤ ቤት አከራዮች ለግለሰብ **ማከራየት አለማከራየት ለመወሰን** ይጠቀሙበታል። የክሬዲት ሪፖርትን መረጃ አካቶ ግን በተጨማሪም **የወንጀል ማህደር** ፣ **ፕራየር ኢቪክሽን እና የቅጥር ታሪክዎን** ያካትታል።

## ማመልከቻዬ በጀርባ ህይወት ምርመራ ምክንያት ወድቅ ተደረገብኝ፤ ምን ላድርግ?

አከራዮ በጀርባ ህይወት ምርመራ ምክንያት በተገኘ እክል ማመልከቻዎን ውድቅ ካደረገብዎ የተጠቀሙበትን ሪፖርት ኮፒ የማየት መብት አለዎት። እንዴት ሪፖርት ማግኘት እንደሚቻል እነሆ፡

**አከራይዎን በጽሁፍ** የጀርባ ህይወት ምርመራ **ያካሄደውን የአገልግሎት ስም ይጠይቁ።**

ድርጅቱን በኢሜል ወይም በፖስታ አማካኝነት በማኘት የርስዎን ሪፖርት ኮፒ ይጠይቁ።

ሪፖርቱን **በጥንቃቄ** ይመልከቱት። በሪፖርቱ ውስጥ የርስዎን መኖሪያ የማግኘት እድል የሚጎዳ ነገር አለ?

**በጀርባ ህይወት ምርመራ ውጤት ምክንያት አከራዮ ማመከቻውን ውድቅ ስላደረገበት ጉዳይ የሚያውቁ ከሆነ ፣ ስለ ጉዳዩ በማብራራት ሃሳባቸውን ሊያስቀይሩ ይችላሉ።**

## የጀርባ ህይወት ምርመራዎ ላይ ስህተት ካለ ማስተካከል ይችላሉ።

በሪፖርትዎ ላይ ክሬዲት ካርድ ታይቷል ምንም እንኳን **የርሶ የሆነ ባይሆንም?** በጀርባ ህይወት ምርመራዎ በወንጀል ተፈዶብዎት እንደሚያውቁ ይናገራል **ምንም እንኳን ሙሉ በሙሉ አስወግደውት ቢሆንም?**

በክሬዲት ሪፖርትዎ ወይም በጀርባ ህይወት ምርመራዎ ላይ ስሀተት ካለ **መርማሪው አካል ጋር የክርክር ቅሬታን በደብዳቤ ማስገባት** ይችላሉ ወይም በድረ ገጻቸው ላይ ቅጽ መሙላት ይችላሉ። **በ30 ቀናት ውስጥ** ከነርሱ ካልሰሙ ወይም **ስህተቱን ለማስተካከል ፍቃደኛ ካልሆኑ፤ ቅሬታዎን የኮንሲውመር ፋይናንሻል ፕሮቴክሽን ቢሮ** ጋር በ consumerfinance.gov/complaint ማስገባት ይችላሉ።

**AMHARIC — CREDIT REPORTS**

LEGAL AID SOCIETY OF MIDDLE TENNESSEE AND THE CUMBERLANDS (833) 837-HOME | AMAC American Muslim Advisory Council (615) 988-6460 | conexión américas (615) 701-7957

ይህ መረጃ ለዴቪድሰን ካውንቲ ብቻ ነው። እዚህ የቀረበው መረጃ የህጋዊ ምክር አይደለም ለመሆንም አይሞክርም። ማንኛውም የህግ ችግር ካሎ የግል ጠበቃዎን ወይም የአቅራቢያዎን የመሃል ቴነሲ እና ከምበርላንድ ቢሮ ህግ ድጋፍ ሶሳይቲ በ 1-800-238-1443 ጋር ይደውሉ. ወይም የናሽቪል ሂስፓኒክ ጠበቆች ህብረት ጋር በ 1-615-701-7957. 9/23 የተሻሻለ።